የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፰ አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 48 ADDIS ABABA, 22th May, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፱/፪ሺ፲፯

የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.............................ገጽ ፲፰ሺ፬፻፷

**Content**

Proclamation No. 1379/2025

Africa Finance Corporation Establishment Agreement Ratification Proclamation ……………………………………Page 18460

## አዋጅ ቁጥር፩ሺ፫፻፸፱/፪ሺ፲፯

## የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ስምምነትን ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ

የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ስምምነት እ.አ.አ ሜይ ፳፰ ቀን ፪ሺ፯ ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ባካሄደው ፳፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፱/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ተዓቅቦ

፩/ የኢትዮጵያ መንግሥት አመቺ በሆነና በመረጠው ጊዜ የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን አክሲዮኖችን ሊገዛ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1379/2025

## AGREEMENT ESTABLILSHLILNG THE AFRICA FINANCE CORPORATION RATIFICATION PROCLAMATION

**WHEREAS**, the Agreement Establishing the Africa Finance Corporation was entered in to force as of the 28th day of May 2007;

**WHEREAS**, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on 29th day of 13th May 2025;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the “Africa Finance Corporation Establishment Agreement Ratification Proclamation No. 1379/2025.”

### 2. Reservation

1/ Ethiopia reserve the right to subscribe for shares in Africa Finance Corporation at its own discretion and preferred time.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን የኢትዮጵያ መንግሥትን ይሁንታ ሳያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የፋይናንስ አቅርቦት ክልከላ ለተደረገበት ድርጅት ወይም ፕሮጀክት የፋይናንስ አቅርቦት ሊያቀርብ አይችልም፡፡

**፫. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፬. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**
**ታዬ አጽቀሥላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

2/ Africa Finance Corporation shall not finance an enterprise or provide for the financing of a project in the territory of Ethiopia if the Government of Ethiopia objects to such financing. To this end, Africa Finance Corporation shall seek the Government's "no-objection" before undertaking its investment.

**3. <u>Ratification of the Agreement</u>**

Africa Finance Corporation Establishment Agreement is hereby ratified.

**4. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake, in cooperation with the concerned government organs, all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**5. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 22 th day of May 2025**
**TAYE ATSEKE SELLASSIE**
**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**